# አዲስ የተመሰረው ትብብር ለዴሞክራሲና ለነፃነት፤ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት በሚደረገው ትግል ላይ  ምን እንደምታ አለው?

ከዋሲሁን መርሶ

ትብብር ለዴሞክራሲና ለነፃነት መመስረቱን ዜና ስሰማ፤ አሁን በመካሄድ ላይ ያለውን ህዝባዊ አመጽ ይበልጥ በተጠናከረ የጋራ አመራር ያቀናጃል ያስተባብራል በሚል ግምት እንደማኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደስ ነበር ያለኝ። ስለትብብሩም የወጡትን የድጋፍና የተቃውሞ መግለጫዎች፤ ትችቶች በጥሞና በመከታተል፤ እኔም እንደአቅሜ ጉዳዩን ማውጠንጠን ጀመርኩ። በማስከተልም የትብብሩ መስራቾች የተፈራረሙበትን ሁለት ሰነዶች እጄ ገብቶ ከአነበኩትና ከመረመርኩት በኋላ ደስታዬ ወደ ሀዘን ተቀየረ።

አዲሱ ትብብር አንድ አመት በላይ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ አመፅ ያዳክመው ይሆን ብዬ ፍራቻ አደረብኝ። እንደው ለመሆኑ ልቦና አግኝተን ከስህተታችን የማንማረው ለምን ይሆን ብዬ በተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር አባላት ላይ አማረርኩ። የአገራችን የፖለቲካ አካሄድ በደፈናው እንቆቅልሽ ሆነብኝ። እረፍት ከነሱኝ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ለምን የብሄራዊ አጀንዳ ማለት ስለአንድነትን፣ ስለአገራችን ህልውና ልዑላዊነት፣ ለሁሉም የምትሆን ኢትዮጵያ ተብሎ በሰነዱ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት ያልሰፈረው? የትብብሩን ሰንዶች እንደተረዳሁት ከወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ጋር በሰላማዊ መንገድ በመደራደር አሁን ያለውን ሕገ መንግሥት ተቀብሎ አዲስ መንግሥት ማቅቋቋም ነው። ታዲያ ይህ አካሄድ ከብሄራዊ አጀንዳ ማለትም የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥትን ሥርዓት መመስረት ጋር እንዴት ይጣጣማል? አይ የእኛ ነገር "ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል" ብዬ አዘንኩ።

ከጭንቀቴ ትንሽ እረፍት ለማግኘት ብዬ ሙዚቃዎች ሳዳምጥ የቴዲ አፍሮ ዘፈን ያስተሰርያል የሚለውን ዘፈን በማዳመጥ ተጽናናሁ ብቻዬን አይደለሁም ብዬ ተሰፋዬ ተንሰራራ። ቴዲ የሚለው “የምንመኘውና የምንፈልገው ለውጥ ገና አልመጣም። ከንጉሱ እስከ ወታደር አሁንም ኢህዴግ ሁሉም መንግሥቶች አምባገነን ናቸው”። እግዚአብሄር ይባርክህ ወይ ነዶ ሁሉም እንዳተ እውነቱን ለመናገረና የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ አገራችን ከጥፋት ለማዳን ቆርጠ መታገል ማታገል አለበት ብዬ ተመኘሁ። ስለዚህ የተቃዋሚ ጎራ በአንድ ልብ፤ በአንድ መንፈስ ሆነን በጋራ ህብረት ያለውን አምባገነን መንግሥት አስወግደን ዴሞክራሲያዊ ሕገ ሥርዓት መፍጠር አለብን ማለት ነው። አሁን ያለንበት ሁኔታ ድርጅቶች “እኔ እበልጣለሁ” ብለው የሚኩራሩበትና የሚፎካከሩበት ጊዜ አይደለም። ተባብረን አገራችን ከጥፋት አድነን የዴሞክራሲዊ ሥርዓት ማምጣት ከተሳነን፤ እንደፈረኝጆች አባባል ከፈረሱ በፊት ጋሪው ይቀድምና ለአራተኛ ጊዜ እራሳችን ለአምባገነን መንግሥት

እናመቻቻለን እንፈቅዳለን ማለት ነው። የተከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ መና ሆኖ ይቀራል ትግሉም ለጊዜውም ቢሆን ይዳፈናል ማለት ነው። እባካችሁ አዛውንት ምሁራን እንዲሁም የሲሽክ ማህበራት አገር ሲጠፋ አንድነታችን ሲናድ ዝም ብላችሁ አትመልከቱ ምክራችሁን ለፖለቲከኞች ለግሱ።

በትብብሩ ሰነድ ላይ ፊርማቸውን ያስፈሩት ድርጅቶች አሁን ያለውን ሕገ መንግሥት እንዳለ እንቀበላለን ሲሉ ያንድ ድርጅት ፕሮግራም ማለት የወያኔ መሆኑን ሊያጤኑት ይገባል። በእኔ እይታ ይሆናል ብዬ የጠበቅሁት ከግንቦት እስከ ግንቦት የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አመፅ ትብብሩ የሚያቀነባብር የሚያፋፍምና ለትግሉም አቅጣጫ በመስጠት የታሰሩት የፖለቲካ ድርጅቶች አመራርና ደጋፊዎች እንዲሁም የነፃ ጋዜጠኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ለማስፈታትና የተሰረቀውን የሕዝብ ድምፅ ለማስመለስ/ለማስከበር መታገል ነበር። ለስኬታማነቱ ትብብሩ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ማለት የሲቪክ ማህበራትን ያካተተ ተጠርቶ ወያኔን በሁለገብ ትግል ለማስወገድ ቆራጥ አቀዋም ላይ መድረስና፤ ከወያኔም በኋላ በሽግግር መንግሥት አማካኝነት የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት በማርቀቅ ወደ መድበለ ሥርዓት ማምራት ይሆናል የሚል ነበር። የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎቻችን ሕብረተሰባችን ያሳተፈ የተቀናጀና የተባባረ የትግል መርህ ግብር ቀይሰው ሥርነቀል የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ጥረት ከማድረግ ፋንታ በሆነው ባልሆነው መራኮቱ በጣም ጎጂና ማንንም የማይጠቅም መሆኑን ለማንም ቅን አገር ወዳድ ድብቅ አይደለም።

ምሁራንም የሚጠበቅባቸውን የትግል አቅጣጫ ጠቋሚ ምርምር/ጥናት ማድረግ በብቃት ገና አልተወጡም፤ ይባስ ተብሎ አንዳንዶቹ በትግሉ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለማፍስ ሲዳዳቸው እየተስተዋለ ነው። እዚህ ላይ ሳይበዛ አንድ የታዘብኩትን ላጋራችሁ። ለጊዜው ምሁር ነን ባዮች ነፋስ ወደ ነፈሰበት የሚነጉዱትን ስለትብብሩ የፃፉትን ውዳሴ ከንቱ ትችት ወደ ጎን ልተውና፤ አንድ የማከብራቸው ፕሮፌሰር ለትብብሩ በጻፉት ድጋፍ በጣም ቅር መሰኘቴን ነው። እንዴት ሰነዱ ለሕዝብ ይፋ ሳይደረግና ነገሩ ሳይብላላ ሙሉ ድጋፍ በችኮላ ሰጡ ብዬ ተጨነቅሁ። አዛውንት ለመዘርጠጥ ፍላጎት ባይኖረኝም ጉዳዩ የአገር በመሆኑ ችላ ልለው አልፈለግሁም። ምናልባት እሳቸው የሚውቁት እኔ የማላውቀውና ያልተረዳሁት ነገር ይኖራል በማለት እንቅልፍ እስከማጣ ድረስ እራሴን አስጨነቅሁ፤ የትብብሩ ሰነድ አሁን በቀረበው መልክና ይዘት የትም አያደርስም።

ፕሮፌስሩን ምንም በአካል ባለውቃቸውም ጥሎብኝ የጽሁፋቸው አድናቂ ነኝ በተለይ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሪቪው በኋላ ደግሞ በኢትዮጵያ ሬጅስተር ላይ በተከታታይ ስለኢትዮጵያ አንድነትና ታሪክ በጻፉት ብዙ ትምህርት ያገኘሁበት ነው። ሆኖም ወደኋላ ላይ አንዳንድ ጽሁፎቻቸውን በተለይ ስለብሄር ብሄረሰብ ችግሮችና መፍትሔዎች ብለው የሚስነዝሩትን ብዙም አይጥመኝም፣ አሳባቸውንም

አልጋራውም። እንዲህ ስል ፕሮፌሰሩ የራሳቸውን ነጻ አስተሳሰብና አቋዋም እንዲሁም የፈለጉትን ድርጅት የመድገፍ መብታቸውን በማክበር ነው። መብታቸው እንደተጠቀ ሆኖ በእኔ እምነት በእሳቸው ደረጃ ያለ አንድ ብድን/ድርጅት ሲያጠፋ በተለይ የአገር ህልውናና አንድነታችንን አድጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲፈጠር ያለአድልዖና ያለይሉኝታ ጥፋተኛውን መምከርና መገሰፅ አለባቸው ባይ ነኝ።

ለትዝብቴ መንደርደሪያ የሆነው ቀደም ሲል ከግንቦቱ ምርጫ በፊት የሚደግፉት መኢአድ ድርጅት በኋላ ከሌሎች ሶስት ድርጅቶች ጋር በመዋሃድ ቅኝጅት ፓርቲ የሆነው፤ የብሄረሰብ ድርጅቶችን ያውም በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና ለመብታቸው ለእኩልነት ለፍትህ የሚታገሉትን ለምሳሌ እንድ ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ድርጅት አማርኛን የኦፊሴል ብሄራዊ ቋንቋቸው ያደረጉትን ዓይናችሁን ለአፈር መባሉና የእነሱም የትግል አጋር የሆኑትን የሕብረብሄር ድርጅቶች ማለት የኢዴሳን አባላትን እንድባላንጣ ተደርገው ይታዩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ያም ሆኖ ለእኔ ዱብ እዳ የሆነብኝ እንዴት በኢትዮጵያ አንድነት ለማያምኑ ወይም በኢትዮጵያዊነት ላይ ወደፊት እንደራደራለን ለሚሉ የብሄረሰብ ድርጅት (ቶች) ሙሉ ድጋፍ መስጠቱ ነው። መቼም የፕሮፌሰሩ ነገር ሆነውብኝ ነው እንጂ ሌላ እንደኔ ያለ ተራ ሰው ቢሆን ኖሮ ቡዙ ባልኩ ደስ ባለኝ ነበር። እስቲ ወገኖቼ ፍርድ ስጡ የወኔስ ቢሆን ምን አጠፋ? ሕገ መንግሥቴን ተቀበሉና በእኔ አስመራጭ ኮሚቴ ደንብና አስተናባሪነት ምርጫም ቢሆን መካፈል ትችላላችሁ አይደለም ወይ ያለው? ይህ አድራጎት ለእኔ የሚመስለኝ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው። የተሰማኝን ሳልፈራና ሳልቸር በመግለፄ እንዲሁም ስለድፍረቴ ይቅርታ በማለት ወደፊት በትግላችን በኢትዮጵያ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ተመስርቶ ለመወቃቀስ ያብቃን በማለት ወደ ዋናው ርዕሴ እመለሳለሁ።

ከግንቦቱ ምርጫ የምንማረው ትልቁ ቁም ነገር ወያኔ አጭበርብሮ ቢያሸንፍም ቢሸነፍም ከሥልጣን ለመውረድ ፍላጎትም ሆነ ፈቃደኛነቱ የሌው መሆኑን ነው። ምርጫው እንዲደረግ የፈቀደው እንዳለፈው ሁለት ምርጫዎች አምታትቼ አሸንፋሁ፤ እግረ መንገዴንም ለዓለም ሕብረሰብ ዴሞክራሲያዊነቴን አሳያለሁ ከሚል ግምትና ስሌት ነበር። በምርጫው በተለይ በአዲስ አበባ ያልጠበቀው ሽንፈት ስለአጋጠመው ሕገ መንግሥቱን ጋሻና መከታው በማድረግ አሸናፊዎቹን የተቃዋሚ አመራር አባላትና ነፃ ጋዜጠኞችን በአገር ክህደትና ሕገ መንግሥቱን በመናድ በሚል ተልካሻ ክስ ወህኒ ቤት ወረወረ። የሕዝብ ድምፅ ይከበር፤ የታሰሩት መሪዎቻችን ይፈቱ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ የወጣውን ሕዝብ ወጣት ሽማግሌ ባልቴትና እናቶች ሳይለይ በልዩ ሠራዊት በአጋዚ አስጨፈጨፈ። በብዙ መቶ ሺ የመቆጠሩ ወጣትና አዛውንትን እስር ቤት አስገባ። ለዓለም ሕብረተሰብ ዴሞክራሲያዊ መስሎ ለመታየት የነበረው ህልም ከሽፎ የለየለት ተራ ሽብርተኛ አምባገነን መሆኑን አስመሰከረ።

ታዲያ ትግላችን በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አንድ የአመራር አባል እንኳን ሳይፈታ በሰላማዊ መንገድ እንደገና ከወያኔ ጋር እንደራደር ብሎ ነገር ምን ይሆን እንደምታው? በበኩሌ ድምፃችን ይከበር ብሎ ብዙ ሰው የሞተበትን፣ የታሰረበትን፣ የተሰደደበትን ከቦታው የተፈናቀለበትንና ንብረቱን ያጣበት ሕዝባዊ አመፅ ወደ ጎን ትቶ የተሸነፈውን ወያኔን እንዳሸነፈ ተደርጎ እውቅና እንደመሳጠት የሚያስቆጥር ይመስለኛል። ሀቁ ይህ ከሆነ ዘንዳ የትብብር ለዴሞክራሲና ለነፃነት ድርጅቶች ከወኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ማለት እራሳቸውን ታማኝ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅት ብለው በፓርላማ ወንበር ከያዙት በምን ይለያሉ? በእኔ አስተያየት ወያኔንም ሆነ ተለጣፊዎችን ለይተን የምናወግዝበት ምክንያት አይታየኝም። በደፈናው "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" ዓይነት ነው፤ እኛ ሥልጣኑን ከያዝን ሁሉም ችግሮች ይፈታሉ ለማለት ከሆነ ስህተት ነው። የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር የፖለቲካ ትርፍ ያገኙ መስሎአቸው በቀላሉ ከማይወጡት አረንቋ ውስጥ መግባታቸው ያሳዝነኛል። ዴሞክራሲ፣ ነፃነት፣ ሰላም፣ እድገት የሚመጣው በስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ማሰብ ወይም መከጀል ለእኔ የሚሆንብኝ እንደው አዬ ሞኙ "በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ" ነው።

የወያኔ ሕገ መንግሥት ሕዝብ ያልመከረበት ያልዘከረበት በግድ ጫንቃው ላይ የጫነበትና ለከፋፍለህ ግዛ እንዲያመች ተደርጎ የተሰናዳ ነው። በአለፉት አስራ አምስት ዓመታት ያገኘነው ተመክሮ እንደሚያሳየን በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተ ፌደራላዊ መዋቅር/ክልል ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝነ፤ ተከባብሮና ተቻችሎ የኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለግጭትና ለብጥብጥ የሚጋብዝና በአጠቃላይ የአገሪቱን ህልውና የሚፈታተንና አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን የተገነዘብነው ጉዳይ ነው። የፌደራል አወቃቀር/ክልል ማለት የሕገ መንግሥት ዋነኛ አካል እንደው በዘፈቀደ ለፖለቲከኞች እንዳሻችሁ አድርጉ ተብሎ የሚተው ጉዳይ አይደለም። መሆን ያለበት ወደፊት የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ሲረቀቅ ሕዝብ መክሮበት ዘክሮበት በሚመርጣቸው ተወካዮቹ አማካኝነት የሚወሰን ትልቅ ጉዳይ ነው። በእኔ እይታ አንድ ውጥ የሆነ ማለት በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተ ክልል በቂ አይደለም። ቢያንስ ሁለትና ሦስት ሞዴሎች መሆን አለበት ባይ ነኝ፤ ምክንያቱም ሁኔታዎች የሚደራረቡበትና የሚደባለቁበት አሉ ለምሳሌ የአፋርና የቀድሞይቱን የትግራይ ክፍላተ አገር ዓይነት ለማለት ነው። የወደፊቱ የዴሞክራሲያዊ ፌደራል አወቃቀር ቋንቋን ባህልን ታሪክንና የኤኮኖሚ ጠቀሜታን ያካተተ ቢሆንና ከሁሉም በላይ የሕዝብን ይሁንታና አመኔታ ያገኘ ቢሆን ውጤቱ ያማረ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

በትብብሩ ሰነዶች ላይ በተደጋጋሚ ነፃነት የሚለው ቃል ሰፍሮ ይገኛል። መቼም አሳቡ ከባርነት ነፃነት ይመረጣል ማለት አሁን ካለው የአምባገነን ሥርዓት እንላቀቅ ከሆነ እሰዬ እንበርታ ነው። ከዚያ ውጭ ነፃነት የሚለው ከአበሻ ቅኝ ገዢነት ነፃ መውጣትን አንፀዖት ለመስጠት ከሆነ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ትርፉ የሚሆነው እንደገና ያለአስፈላጊ የእርስበርስ ጦርነት ሕዝባችን

መጋበዝና የመከራ ዘመኑን ማራዘም ነው ። ይህም እንደ ዘመነ መሳፍንት አባቶቻችን በታሪክና በልጅ ልጆቻችን የሚያስወቅሰን ይሆናል። ትብብሩ ነፍስ እንዲዘራና ይበልጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከተፈለገ የነፃነት ትርጉሙን በንድፈ አሳብ ደራጃ መዳበርና ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው። እኔ እንደሚገባኝ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የነፃነት ጥያቄና ትግል ከዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ምስረታ ጥያቄ ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነው። የትግላችን አቅጣጫ መሆን ያለበት ብዬ የማስበውን ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ። የግለሰብና የቡድን (የብሄረሰብ) የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ማስከበር። እንዲሁም ሁሉም አገሪቱ ዜጎች የመሰብሰብ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመድራጀት ከዚህ በተጨማሪ ዜጎች በአገሪቱ ውስጥ እንደልብ መዘዋወር በፈለጉት ቦታ መኖር መሥራት፣ ሃብት ማፍራት የመቻልን ነፃነትና መብት መኖሩን ማስረገጥ ነው። በአጠቃላይ ለሁሉም የምትሆን ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ማለት በፖለቲካው በኤኮኖሚው በማህበራዊ ጉዳዮች ማለት ፖሊሲዎችን ሕዝባችን በውክልና በሚመርጣቸው አማካኝነት በአንድነትና በእኩልነት በፍትሃዊ መንገድ በማውጣትና በማስፈጸም አገራችን ከወደቀችበት አስከፊ ሁኔታ ማንሳት የዜግነት ግዴታችን ነው።

ማጠቃለያ

ይህ መጣጥፍ ትኩረት የሰጠው አዲስ በተቋቋመው ትብብር ለዴሞክራሲና ለነፃነት ላይ ነው። የትብብሩን ሁለት ሰነዶች ደካማ ጎኖችን በጊዜ እንዲታረሙና ሉብሄራዊ አጀንዳ ቅድሚያ እንዲሰጥና ብሄር ብሄረሰብ አጀንዳና የፖለቲካ ድርጅቶች ሽኩቻ በዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ሥርዓት ውስጥ እንዲሆን ለማሳሰብ ጥረት አድርጓል። የጸሁፉ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያዊነት ማለት አንድነት በልዩነት ማለት ፌዴራሊዝም በዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አማካኝነት ለችግሮቻችን መፍትሔዎች መላ ምት ለማፈላለግ ነው። አንድ በእርግጠኝነት መነገር ያለበት የአለፉት ሥርዓቶች በንጉሡም ሆነ በወታደራዊ መንግሥትም የብሄር ብሄረሰብ ጭቆና ብዝበዛና የሰብዓዊ መብት ለገጣ ነበረ፡ አሁንም በወያኔ/ኢህአደግ መንግሥትም በተጠናከረ መቀጠሉን ነው። በጽህፊውና በአክራሪ ብሄርተኞች መካከል ያለው ልዩነት ችግሮቻችን እንዴትና መቼ በቅደም ተከተል እንፍታው የሚለው ላይ ነው። እንደፀሃፊው አስተሳሰብ የብሄራዊ አጀንዳ ይቅደም ማለትም ኢትዮጵያዊነት የአገር ህልውና አንድነት ለማለት ነው።

አገራችን የብዙ ብሄረሰቦችና ሃይማኖቶች ያሉባት ጉራማይሌ አገር ናት። እሩቅ ሳልሄድ የእራሴን የትውልድ ሐረግ ስመረምር ከቅድመ አያቴ ጀምሮ ከኦሮሞዎች ጋር በጋብቻ የተሳሰርኩ ነኝ። ቀሪዎቹ ዘመዶቼ ከትግሬ፣ ከጉራጌ፣ ከወይላታ፣ ከኤርትራ ጋር የተጋቡና የተዋለዱ ናቸው። አብዛኛዎቹ ዘመዶቼ ሁለትና ሦስት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አቀላጥፈው ይናገራሉ። እኛ ቤት ልዩነታችን ጌጣችን ነው። የሚያስተሳስረን አንድነታችን ኢትዮጵያዊነት ነው። ይህ በአገር ደረጃ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም፤ የምዝበራውና የጭቆናው ዓይነትነትና መጠን ይለያይ

እንጂ ሁላችንም የነበሩትና ያለው ሥርዓት ስለባ ነን። ስለዚህ በህብረት ትግል ሥርነቀል የሥርዓት ለውጥ ማምጣት አማራጭ የለውም ጉዳይ ነው። ስለ አገሬ ይበልጥ አድማሴን ያሰፋልኝ ነገር በወጣትነቴ የሕዝብ ቀጠራ መ/ቤት በመስራት አራቱን ማዕዘን ማለት ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ እንዲሁም ከምዕራብ እስከ ምስራቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ አኗኗር ባህሎች ልዩነትና አንድነት ለማየትና ለመማር እድል ማግኘቴ ነው። አንድ የተማርኩት ትልቅ ቁም ነገር ሕዝባችንን ከሚያለያዩት ልዩነት ይልቅ የሚያስተሳስሩትና የሚያስማሙት አንድነት አመዛኝ መሆኑን ነው። ሕዝባችን በረጅም ታሪኩ የውጭ ውራሪዎች በተባበረ ክንዱ ድል በመምታት ነፃነቱን ጠብቆ ለመኖር በቅቷል። ያለ መታደል ሆኖ ከመለኮታዊ ሥልጣን ወደ ወታደራዊ አምባገነን አሁን ደግሞ ያለንበት የዘረኛ አምባገነን መንግሥት ስር ወድቆ ይገኛል። የእራሱን ሕገ መንግሥት ለመቅረፅና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት የሞትና የሽረት ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል።

ያለመታደል ሆኖ የ66ቱ የአብዮት ፍሬ በወታደራዊ አምባገነን መንግሥት ተነጠቀ። ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት ሕዝባችን ገና አልነቃም አልተደራጀም አልታጠቀም እስክዚያ በሞግዚትነት አገሪቱን አስተዳድራለሁ በማለት ሥልጣንን ላይ የሙጥኝ አለ። ይህን የተቃወሙ የሕብረብሄር ድርጅቶች በተለይ ኢህአፓን የጥቃት ዓላማው በማድረግ በቀይ ሽብር የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎችን ጨፈጨፈ። የዚህ ድርጅት ኅጢአት “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፤ ዴሞክራሲ ያለገደብ” ለሕዝባችን ይሰጥ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣቱ ነበር። የጉዱ ጉድ የዚያ ሥርዓት አባሪ ተባባሪ የነበሩ ጥፋታቸውን ለመደበቅ “ኢህአፓ ወጣቱን አስጨረሰው” በማለት አጥቂውን ትተው ተጠቂውንና ተበዳዩን ይወቅሳሉ። ታዲያ ለመጣው ሁሉ አምባገነን አደግዳጊ የሆኑ ሆድ አድሮች አሁንም በተራቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይ ቅንጅትን ሕዝቡን አስጨረሱት ቢሉ ምን ይገርማል። ዳኝነቱን ጤነኛ አዕምሮ ላለውና ለለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊ እተወዋለሁ።

የወታደራዊ አምባገነን መንግሥት የህብረብሄር ድርጅቶች በማዳከሙ የብሄርተኛ ድርጅቶች ማለት ወያኔና ሻቢያ እንዲጠናከሩ ረድቷል። በመጨረሻም የወታደራዊ መንግሥት በእራሱ ቀውስ ሲገረሰስ ወያኔ ከተለጣፊዎች ጋር በመሆን ኢህአዴግ ነኝ በማለት አዲስ አበባን ሻቢያ ደግሞ አስመራን ለመቆጣጠር በቁ። በአለፉት አስራ አምስት አመታት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ያለፍላጎታቸው መለያየታቸው አንሶ፤ የደረሰባቸውን መከራ ጦርነት፤ ረሃብ፤ መፈናቀልና መሰደድ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ወደፊትም በሁለቱም አገሮች ዴሞክራሲያዊ መንግሥቶች ሲመሰረት ተመልሰው አንድ እንድሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን ግን ልንጠነቀቅ የሚገባን ነገር ለአራተኛ ጊዜ ሌላ አምባገነን እንዳይመጣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት አጥብቀን መታገል እንዳለብን ነው።

በቅርቡ የተቋቋመው ትብብር ለዴሞክራሲና ለነፃነት መልካም ጅማሮ መሆኑን በማጤን በመካሄድ ላለው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ላይ አወንታዊ እንደምታ እንዲኖረው የሚከተሉትን እጠቁማለሁ።

1- የተቃዋሚ ድርጅቶች/ሃይሎች የትብብሩን ሰነዶች የፈረማችሁና ያልፈረማችሁ በመካከላችሁና በደጋፊዎቻችሁ መካከል ያላስፈላጊ መቃቃር ሥር ከመስደዱና እንድው በጭራሽ መተማመን ከመጥፋቱ በፊት በሰከነ አዕምሮ፣ በቅንነትና አላፊነት በተሞላበት መንገድ ሰነዶቹን በዴሞክራሲያዊ አሰራርና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በመደራደር እርምት በማድረግ ሁሉን የሚያስማማና ትግሉን የሚያጠናክር ሰነዶች ማውጣትና ሕዝባዊ አመፁን እንዲቀጥል አቅጫ በመስጠት ታግሎ ማታገል ማድረፍ ይገባቸዋል።

2- አዲሱ ትብብር በማያሻማ የወያኔ መንግሥትን፣ ሕገ መንግሥቱንና ሥርዓቱን ለማስወገድ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ማለትም የሲቪክ ማህበራትን በማካተት የትግል መርሃ ግብር በቅደም ተከተል በመንደፍ ትግሉን ማፋፋም አስፈላጊና ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑን እንዲያጤኑት ያስፈልጋል።

3- ከወያኔ በኋላ ለሚቋቋመው ሁሉን አቀፍ ማለት የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች ያካተተ የሽግግር መንግሥት ማለት ከአለፈው የወታደራዊ መንግሥትና የኢህአዴግ መንግሥት ምስረታ ስህተቶች እንዳይደገሙ ጥንቃቄና ትምህርት በመውሰድ የሽግግር መንግሥትን ዓላማና ግቡን በግልፅ ማስቀመጥ፤ ዋና ተግባሩም የዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥትን ማርቀቅ፤ የፈራረሱ የኤኮኖሚና የባህል ተቀዋሞችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ተቀዋምነት መለወጥ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ መጨመር ተገቢ ነው። የሽግግር መንግሥት ሊያስራው የሚችል መተዳደሪያ/ቻርተር አፅድቆ ለዚያ ተገዢ መሆን። በአገሪቱ ሰላምና እርቅ በማድረግ መረጋጋትን መፍጠር። የሽግግር መንግሥቱም በሥልጣን የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥና ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት።

4- የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከተመሰረተ በኋላ ፖለቲካው ለፖለቲካ ድርጅቶች ይሰጣል፤ የሲቪክ ማህበራት ደግሞ የራሳቸውን የሙያ ማህብራት የአባላትን ጥቅም ማስገኘትና ማስከበር እንዲሁም የሕገ መንግሥቱና የዴሞክራሲያዊ ሙብቶች ተከራካሪነትና ጠባቂነት ይሰማራሉ። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ድርጅቶች "እኔ ነኝ ቅንጆ" በማለት ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ በማስተዋወቅ ለሥልጣን ማለት የሕዝብ አገልጋይ ለመሆን ይወዳደራሉ፤ ያቸነፈው ፓርቲ ለተወሰነ ጊዜ አገሪቱን ያስተዳድራል ተሸናፊው(ዎቹ) ደግሞ በምክር ቤት ወይም በፓርላማ ውስጥ ታማኝ ተቃዋሚ ሆነው አወንታዊ ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው።

በአጠቃላይ የአገራችን የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ መወስን ያለብን እኛው እራሳችን ነን። የውጭ ጣልቃገብነትን መፍቀድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡ መዘዙም ብዙ ነው። ሁሉም አገር የሚሰራው ከእራሱ ጥቅም አንፃር ነው። ይህኛው ያኛው እንዲህ ያረግልናል ብለን እራሳች አናጃጅል። በአለፉት አስራ አምስት ዓመታት ተመክሮአችን ለባዕዳን ሃይሎች ደጅ መጥናቱ ፍሬ አልባ መሆኑን የተገነዘብነው ጉዳይ ነው። ስለዚህ በቁርጠኝነት በሁሉም መስክ መታገልና አቸናፊ ሆነን መውጣት አለብን። ያኔ የውጭ ሃይሎች ሳንጠይቃቸው ለራሳቸው ሲሉ ድጋፍም እርዳታም በገፍ ያቀርባሉ። እግዚአብሔር ለፖለቲካ ድርጅቶች አመራር አባላት ልበስፊነትን አስተዋይነትንና አርቆአሳቢነትን ይለግሳቸው፤ እንዲሁም አገራችን ኢትዮጵያን ከክፉ ነገር ይጠብቃት። አሜን።